# እውን ተቃዋሚዎች ለሕጋዊና ሰላማዊ ፖለቲካ ተዘጋጅተዋል?

*(ከዳግማዊ 07/04/09)*

*ለአራተኛ ጊዜ ምርጫ ለማካሄድ እየተዘጋጀን ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ሦስት ምርጫዎች አካሂደናል፡፡ ላለፉት አሥራ አምሥት ዓመታት በሕዝብ ድምፅ የተመረጠ መንግሥት ሊኖራት የቻለችው አገራችን በዚህ መንገድ ከቀጠለች ሥልጣን ከጠብመንጃ አፈሙዝ ወይም ከጐዳና ነውጥ የሚፈልቅባት አገር ከመሆን በጣም ትርቃለች፡፡ አራተኛው ምርጫ በሚቀጥለው ዓመት ሲካሄድ ሂደቱ ዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊና ከማንኛውም ግርግር የፀዳ እንዲሆን ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይመኛሉ፡፡*

*የመላ ሕዝብ ፍጐትና ምርጫ የገነነበት ሰላማዊ ምርጫ ሲነሳ በመልካም አርአያነቱ ቀዳሚ ተጠቃሽ ከሆኑ አገሮች ውስጥ የአህጉራችን አካል የሆነችውና ከረዥም ዘመናት ሲያርዳት ከቆየው የማኅበራዊ ግጭት ተላቃ ለአራተኛ ጊዜ ሰላማዊ ምርጫ በስኬት ያጠናቀቀችው ደቡብ አፍሪቃ አንዷ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ታዲያ በደቡብ አፍሪካ ለአራተኛ ጊዜ የተካሄደው ይህ ምርጫ በሰላም ለመጠናቀቁ ዋነኛው ምክንያት የሁሉም ማኅበረሰባዊ ቡድኖች ቁርጠኝነት ከሆነ በኛም አገር የሚካሄደው ምርጫ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሊሆን የማይችልበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም፡፡ ነገር ግን በደቡብ አፍሪካ የሆነ መልካም ነገር ሁሉ እኛም ዘንድ ሊሆን የሚችለው መና ከሰማይ በመጠበቅ እንደማይሆን ግልፅ ነው፡፡ ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በመታገል እንጂ፡፡*

*በኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ከተካሄዱት ምርጫዎች ሁሉ በተወዳዳሪነትም ሆነ በግጭት ገፅታው የሚታወቀው በ1997 ዓ.ም የተካሄደው ሦስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ነበር፡፡ ይህ ምርጫ በገዥውና ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ነበር፡፡ ከ16 በላይ ቀጥተኛ የሚዲያ ሽፋን ያገኙ ክርክሮች የተካሄዱበት የ1997 ምርጫ የድምፅ ውጤት እስከተገለፀበት ጊዜ ድረስ ከፉክክር በቀር አንዳችም ግጭት*

አልታየበትም፡፡ ይህ የሆነው በግጭት አቅጣጫ የሚመራ ፓርቲ ስላልነበረ አይደለም፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በሕገ-መንግሥቱ መሠረት የተበጀውን የምርጫ የውድድር ሂደት ኢ-ሕገ-መንግሥታዊ በሆነ መንገድ የሥርዓት ለውጥ የሚያስከትል ሕገ-ወጥ አመፅ መቀስቀሻ ለማድረግ አቅደው የተንቀሳቀሱት ተቃዋሚዎች ገና ከጠዋቱ ራሱን ዴሞክራሲያዊውን የምርጫ ሂደት በማዋደቅና በማጥላላት ለአመፅ ዝግጁ የሆነ ሥነ-ልቡናዊ ሁኔታ በሕዝቡ ውስጥ ለመፍጠር አስበው ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ይህን የአመፅና የአድማ ስትራቴጂ ይዘው ከቀረቡበት ከሐምሌ 1996 ዓ.ም ጀምሮም የአመፅ ቀረርቶ ተለይቶን አያውቅም፡፡ ይህ የአመፅ ቀረርቶ የቅንጅት መሪዎች በቆሰቆሱት አመፅ ምክንያት በቁጥጥር ሥር ውለው በሕግ እስከተጠየቁበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ ነበር፡፡ ከድምፅ መስጫው እለት በፊት ፈልገውት የነበረው ግጭት ያልተቀሰቀሰው መንግሥት የአመፅን መንገድ ለማስቀረት በሩን ከመቸውም ጊዜ በላይ ወለል አድርጎ ስለከፈተው ብቻ ነበር፡፡ የዴሞክራሲው ስፋት ለአመፅ የሚሆን ሰበብ እንዳይኖር በማድረጉ የአመፃ ኃይሎች ያለውዴታቸው በሰላም ከመወዳደር ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡

የምርጫው ቆጠራ ተጠናቆ ውጤቱ ከተገለፀ በኋላ ግን ውድድሩ አብቅቶ ሥልጣን የሚያዝበት ደረቅ እውነታ ብቻ ፈጦ ቀረ፡፡ ተቃዋሚዎች ከምርጫው ማግስት ያገኙት አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ የማሸነፍ ውጤትና በፌዴራልና በክልል ፓርላማዎች ደግሞ በርከት ያለ ወንበር ነበር፡፡ በአመፅ ሥርዓቱን ከመገርሰስ መለስ ያለ ማንኛውም ነገር ላለመቀበል ያቀዱት እነዚህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዴሞክራሲያዊው የምርጫ ሂደት የተፈጠረውን ይህን ታላቅ ዕድል የመጠቀም ፍላጐት አልነበራቸውም፡፡ ገዥው ፓርቲ በአዲስ አበባ ሽንፈት እንደደረሰበት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ተቃዋሚዎች ከተማዋን እንዲያስተዳድሩ፣ በፓርላማዎች ደግሞ ያገኙትን ወንበር ይዘው እንዲሳተፉ ጥሪ ቢያቀርብም ይህን ለመቀበል ሳይፈቅዱ ቀሩ፡፡ ይልቁንም ‘‘በኃይል የተወሰደብንን ሥልጣን በኃይል እናስመልሳለን‘‘ በሚል መፈክር ለአመፃ ጥሪ አቀረቡ፡፡ በዚህም ምክንያት ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም የመጀመሪያውን አመፅ ቀሰቀሱ፡፡ በዚህ የአመፅ ጥሪ የአዲስ አበባ ከተማ ተናጋች፡፡ መንግሥት ያሳየውን ታላቅ ትዕግሥትና እራስን የመግራት ባህሪይ በተሳሳተ ንባብ እንደድክመት የተረዱት የአመፁ መሪዎች በሕገ-ወጥ ድርጊታቸው ገፉበት፡፡ አመፁ ለሦስት ቀናት የቆየ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ቀን የጐዳናው ነውጥ ተዋናዮች አባራሪ ፖሊስ ደግሞ ተባራሪ የሆነበት ሁኔታ ተከሰተ፡፡

እስከመሆን ደረሰ፡፡ መንግሥት በአመፅ ሥልጣን መያዝ አይገባም ብሎ ያቀረበው ጥሪ ሰሚ ጆሮ በማጣቱ ግርግሩ ከቁጥጥር ውጪ ማምራት ጀመረ፡፡ የድሃው ሕዝብ መገልገያ የሆኑ አውቶቡሶች ተሰባበሩ፣ ተቃጠሉ፡፡ የፖሊስ መኪና ተሰባበረ፣ ተቃጠለ፡፡ የማታ ማታ የመንግሥትም ትዕግሥት መሟጠጥ በመጀመሩ አመፁ አግባብ ባለው ኃይል በቁጥጥር ሥር እንዲውል ተደረገ፡፡

ሕገ-መንግሥታዊ የሥልጣን ሽግግር በሕዝብ ድምፅ እንጅ በይገባኛል ባይነት የማይከናወን በሆነባት አገር የአመፅ ኃይሎች የጠሩት ከሰኔ 1-3 የቆየው አመፅ ተቃዋሚዎችን ወደ ሥልጣን ሳያመጣ በአመፁ መሪዎች ቅስቀሳ የነሆለሉ ዜጐችን ለሞትና ለመቁሰል ዳርጐ ረገበ፡፡ ነገር ግን አመፅን የሥልጣን መያዣ መንገድ አድርገው የያዙት ወገኖች የልባቸው ስላልደረሰና መንግሥት ጉዳዩን ወዲያወዲ ወደ ሕግ የማምራት ፍላጐት አለማሳየቱን በተለመደው ወንጋራ ንባባቸው እንደ ድክመት የወሰዱት ተቃዋሚዎች እንደገና ለሌላ አመፅ ቀጠሮ ያዙ፡፡ ለመስከረም ሃያ አንድና ሃያ ሁለት ዘጠና ስምንት ዓመተምህረት፡፡

የመስከረም 21 ቀጠሮ ከመድረሱ በፊት የቅንጅት የወቅቱ መሪ የነበሩት ኃይሉ ሻውል ከ10-15 ሺህ ሰው ሞቶ መንግሥት ሊወገድ እንደሚችል ግምታቸውን በይፋ ገለፁ፡፡ ቅንጅቶች ለሁለተኛ ጊዜ ሌላ ሙከራ እንደሚያደርጉ ግልፅ ሆነ፡፡ ወደፓርላማ ግቡ ሲባሉ አንገባም አሉ፡፡ አዲስ አበባን ተረከቡ ተባሉ፡፡ ይህንንም እምቢኝ አሉ፡፡ በመጨረሻ ጥቅምት 21 ላይ ሁለተኛውን አመፅ ጠሩ፡፡ አጠራሩ የዋዛ አልነበረም፡፡ ታክሲ ሥራ እንዲያቆም፣ ሱቅ እንዲዘጋ፣ ሰዎች በፖለቲካ ምክንያት ከሚለዩዋቸው ጋር ቀብር እንዳይቆሙ፣ ቡና እንዳይጣጡ በመጥራት የጀመረው አመፅ ብዙም ሳይቆይ ተቀጣጠለ፡፡ እንደገና መኪኖች፣ የሕዝብ ትራንስፖርት አውታሮች ጋዩ፣ የተማሪዎች የፈተና ወረቀት የተከማቸበት የፈተናዎች ድርጅት፣ ቴሌ፣ ወዘተ በእሳት ተንቀለቀሉ፡፡ እንደገና መንግሥት ተባራሪ ነውጠኛ አባራሪ የሆነበት ድራማ ተከሰተ፡፡ መንግሥት ሲብሰበት አመረረ፡፡ ፖሊሶቹ ሲገደሉ፣ የሕዝብ ንብረት ሲጋይ ሥርዓት አልበኝነት ሲበዛ መንግሥት ከምር አመረረ፡፡ አመፁን በእሳት አደጋ መኪና ማቆም ቢያቅተው እሱም ተኮሰ፡፡ አመፁ በቁጥጥር ሥር የዋለው፡፡

ይህ የ1997 አመፅ አጭር ታሪክ ነው፡፡ ታሪክ በመሆኑ ብዙም አያሳስብም፡፡ የሚያሳስበው መጪው ምርጫ ነው፡፡ መጪው ምርጫ ምን ያህል ከግርግር እና ከጦጳና ላይ ነውጥ የፀዳ ይሆናል የሚለው በርግጥም ሁላችንንም የሚያሳስብ ጉዳይ ነው፡፡ አቋሙን በመርህ ላይ የተገነባ ነውና የመንግሥት አካሄድ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው እምብዛም አያሳስብም፡፡ መንግሥት ምርጫውን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ዝግጁነቱ አለው፡፡ በአገራችን ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ልማት ያመጣን መንግሥት በምርጫ ውድድር እረታለሁ ብሎ የሚሰጋበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ በተለይ ደግሞ ብዙም ዋጋ የሚሰጠውና እምነት የሚጣልበት ተቃዋሚ በሌለበት ሁኔታ መንግሥት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ከሥልጣን ልወገድ እችላለሁ በሚል ሥጋት ተሞልቶ የሚዋጥበት ምክንያት እንደማይኖር ግልፅ ነው፡፡ የፓርቲው የኋላ ታሪክም ለዴሞክራሲ ያለውን ቁርጠኝነት በሚገባ የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የአቋም ለውጥ ይኖራል የሚል ሥጋት አይኖርም፡፡ ስለሆነም መንግሥት ምርጫውን እንደተለመደው ዴሞክራሲያዊ ያደርገዋል ብሎ መገመት ከባድ አይሆንም፡፡ ከባዱ ፈተና የሚኖረው ተቃዋሚዎች በርግጥ ለሰላማዊ ምርጫ ተዘጋጅተዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ነው፡፡

ተቃዋሚዎች ለሰላማዊ ምርጫ ተዘጋጅተዋል የሚለው ጥያቄ ከባድ ፈተና የሚደቅነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ በሰላማዊ ምርጫ ጥያቄ ላይ ተቃዋሚዎች ፈፅሞ የማታመን ባህሪ ስለሚያሳዩ ነው፡፡ ዛሬ አፈር ነገ ሰው፣ ከነገ ወዲያ አፈር እንደገና ሰው እየሆኑ በመገለባበጥ ጭራ መጨበጫ የሌላቸው ሆነው በመቆየታቸው አፍ ሞልቶ አቋማቸውን መናገር ያስቸግራል፡፡ ይህን ለማለት የተገደድኩት ከራሳቸው ባህሪ በመነሳት ነው፡፡ አመፃ በጠኑ ማግስት የሕግ ተጠያቂነት ሲመጣ ይቅርታ ይጠይቃሉ፡፡ መንግሥት ሆደ ሰፊ ሆኖ ይቅርታ በሰጣቸውና የነፃነትን አየር መተንፈስ በጀመሩ ማግስት አመፅ ይጠራሉ፡፡ በዚህ ጥፋታቸው በቁጥጥር ሥር ሲውሉ ሌላ የይቅርታ እድል ይጠይቃሉ፡፡ የማያልቅ የአቋም መገላበጥ የሚያሳዩና በእሳት መጫወት የለመዱ ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልክአ ምድር ሞልተዋል፡፡ ሦስተኛ መንገድ እያለ በመውተርተር ላይ ያለው ኢዴአፓ መድህንም ቢሆን ከዚህ የሚያገረሽ የአመፅ ፖለቲካ ሙሉ በሙሉ እንደተላቀቀ የሚያቀርበውን መሀላ ማመን ብፈልግም ፈረንጆች "የመጨረሻው ማረጋገጫ ተግባር ነው" እንደሚሉት በአራተኛው ምርጫ በሽታው እንደማያገረሽበት በግልፅ ማሳየቱን ከመጠበቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አልተወልንም፡፡

*ሌሎቹ ግን አሁንም አፈርና ውሃ እየሆኑ በእሳት ለመጫወት እንደሚፈልጉ ተደጋጋሚ ምልክቶች እያሳዩን ነው፡፡*

*ሰሞኑን ከዚህ አኳያ የተላለፈልን መልዕክት የሰኔ 1 ግርግርን አራተኛ ዓመት መታሰቢያ በማድረግ በተካሄደው ወይም ሊካሄድ የታሰበው ሥነ-ሥርዓት አንዱ ነው፡፡ ሥነ-ሥርዓቱ በመኢአድና አንድነት ፓርቲዎች ጽ/ቤቶች አካባቢ እንደሚከበር የግሉ ሚዲያ አብስሮናል፡፡ የሰኔ አንዱ አመፅ ሕገ-መንግሥታዊ ባልሆነ መንገድ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ባሰቡ ኃይሎች የተካሄደ የወንጀል ድርጊት መሆኑ በነፃ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ የአመፁን ጠንሳሾች ለዕድሜ ልክ እሥራት የሚያበቃ ግዙፍ የወንጀል ድርጊት ነበር፡፡ በመሆኑም ይህን የነውጥ ቀን ማክበር በዚሁ የነውጥ መንገድ እቀጥላለሁ ከማለት የተለየ ትርጉም የለውም፡፡ ይህን የአመፅ ቀን ማክበር በተለይ በፈፀምነው ወንጀል ተፀፅተናል ብለው በምህረት የወጡ የአመፁ መሪዎች ተሰምቶናል ሲሉ ‘‘ልባዊ ፀፀት‘‘ ለማታለል የቀረበ እንደነበረ አመልካች ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመፅን የሚሰብኩ፣ የአመፅን ጥቅም ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ለነገው አመፅ መንገድ እየጠረጉ እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ እንደገና እሳት፣ እንደገና ነውጥ… ሌላ ይቅርታ እስኪጠየቅ ድረስ መሆኑ ነው፡፡*

*ይህ የተለመደ ሆኗል፡፡ ብርቱካን በብርቱካናማው አመፅ ተሳትፋ ወህኒ ወረደች፡፡ ፍርድ ቤት የእድሜ ልክ እሥራት በየነባት፣ መንግሥት በምህረቱ [ይቅርታ ስለጠየቀች] ለቀቃት፡፡ ተመልሳ አልተፀፀትኩም፤ ይቅርታም አልጠየኩም አለች፡፡ ይቅርታውን በማታለል እንዳገኘች ገለፀች፡፡ ላለመድገም ምላ ተገዝታ ከራቀችው ወንጀል ጋር ተቃቀፈች፡፡ የይቅርታውን ሁኔታ ሰብራ ወህኒ ገባች፡፡ አንዳንዶች እንደገና ይቅርታ ብትጠይቅስ ይላሉ፡፡ እሳት ነበረች፡፡ አፈር ብትሆንስ ዓይነት ነው፡፡ አፈር እሳት፣ … እሳት … አፈር እሳት…. የማያቋርጥ ኡደት፡፡ ባልደረቦቿ ሰኔ አንድ የጐዳና ላይ ነውጥ ጠሩ፡፡ መንግሥት ወዮላችሁ ሲል አመፁን ሰርዘናል ብለው እኩለ ሌሊት ላይ አወጁ፣ እንደገና ለሌላ ጊዜ አሳልፈነዋል አልን እንጅ አመፁስ አይቀርም አሉ፡፡ እንደ ዝንጀሮ ጐረምሳ የመንግሥትን ጥንካሬ ሲፈትሹ ከከረሙ በኋላ በወርሐ ጥቅምት አዲስ አበባን እንደገና አመሷት፡፡ መንግሥት ተረባርቦ አመፁን አበረደው፡፡ ነገር ግን ቀጣዩን መስመር ጥሳችኋልና ዘብጥያ ትወርዳላችሁ ብሎ ከሰሳቸው፡፡ በፍርድ*

ቤት ተሚግቶም ጥፋተኝነታቸውን አረጋግጦ የዕድሜ ልክ ቅጣት አስበየነባቸው፡፡ ነገር ግን መደበኛው ቅጣት ሳይጀመር ይቅርታ ስለጠየቁና መንግሥት ለነሱ ሳይሆን ለመረጣቸው ሕዝብ ያለውን አክብሮት ለማሳየት በቅድመ ሁኔታ ላይ በተመሠረተ ይቅርታ ለቀቃቸው፡፡ እነሆ አሁን የይቅርታውን ሁኔታ መስበር ጀምረዋል፡፡ እንደ ወጣት የዝንጀሮ ገመር የመንግሥትን ዱካ እንደገና መለካት ጀምረዋል፡፡ ከአፈር ወደ እሳት … ከእሳት … ወደ አፈር እንደገና ደግሞ ወደ እሳት፡፡

ይህስ የሚሆነው ለምንድነው? ብለን መጠየቅ የአባት ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ለሰላማዊ ፖለቲካዊ ባህሉ፣ ፍላጐቱ፣ ቅርበቱ፣ ዝግጅቱ ስለሌላቸው ነው ብሎ መደምደም ከባድ አይደለም፡፡ እንኳንስ ከመንግሥት ጋር እርስ በርሳቸውም ለሰላማዊ ፖለቲካ ቦታ የላቸውም፡፡ እንኳንስ ከገዥው ፓርቲ ጋር እርስ በርሳቸውም ተቻችሎ መደማመጥ አይሆንላቸውም፡፡ የኢዴፓና የነበረት መሪዎች የጐሪጥ ሲተያዩ ከራርመዋል፡፡ ሰሞኑን ኃይሉ ሻውል በአንድነት የስብሰባ ቦታ በመገኘታቸው ጉድ ሲባል የከረመው በመኢአድና በአንድነት መካከል ሰላም ስለሌለ ነው፡፡ ለሰላማዊ ፖለቲካ ቦታ ከሌለ ገዥ ፓርቲ ከተገኘ ከሱ ጋር ከሌለም ከባልደረባህ ጋር መፋለም አይቀሬ ነው፡፡ አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ለሕግ የበላይነት ያላቸው ጥላቻ ነው፡፡ ወንጀለኛ ተብሎ የተፈረደበት ሰው በተለይ በይቅርታ ወይ በአመክሮ ከተለቀቀ በኋላ ቀጥሎ ማድረግ ያለበት ከጥፋት መቆጠብ ነው፡፡ ተፈርዶበት የታሰረ ወይም የተቀጣ ሰው በምህረት፣ በአመክሮ ወዘተ.. ሲለቀቅ ድጋሚ ከወንጀል ለመራቅ አስቧል ተብሎ ነው፡፡ ተቃዋሚዎቻችን ግን የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አይጠጋቸውም፡፡ በይቅርታ ሲለቀቁ መንግሥትን የሸወዱ ያህል ከባድ ደስታ ይሰማቸዋል፡፡ በዚህ ሥነ-ምግባራዊ ዝቅጠት መኩራራትም ይዳዳቸዋል፡፡ እናም ወንጀል ለመፈፀም መትጋት የሚጀምሩት በአመክሮ በተለቀቁ ማግስት ነው፡፡ አበው ሲተርቱ ‘‘የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማዕድ’’ ይላሉ፡፡ በአመፅ ጥያቄ ላይ የአይጥና ድመት ጨዋታ የሚያካሂዱት ተቃዋሚዎች እነሆ እንደገና የሕጉን ብርታት፣ የመንግሥትን ቁርጠኝነት የሕዝቡን ትዕግሥት ሊፈትኑ ዳር ዳር ማለት ይዘዋል፡፡ አፈር ልሰው ከተነሱ በኋላ እንደገና እሳት ለመሆን የንግግር ባሩድ ማግበስበስ ጀምረዋል፡፡

ለሕግና ለሥርዓት ጥላቻ፣ ለፍርድ ቤቶችና ለምርጫ ቦርድ ሌላ ጥላቻ፣ ለተቋማት ንቀት ወዘተ.. የሚያሳዩ ተቃዋሚዎች እስካሁን ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የረባ አስተዋጽኦ አላበረከቱም፡፡ ድመትን በማበረታታት ወደ ነብርነት መቀየር እንደማይቻለው ሁሉ ተቃዋሚዎችን ካለተፈጥሯቸው ዴሞክራሲያዊ ማድረግ ከባድ መሆኑ አይቀርም፡፡ ቢያንስ ግን ለሕግ የበላይነት እንዲገዙ ማድረግ ይቻላል፡፡ ምርጫ በወጣ ቁጥር ከ10 ሳው ሞቶ እኔ ሥልጣን ላይ እወጣለሁ ብለው የሚያስቡ ሰዎችን በምርጫ ሰበብ የሚሞትም፣ ሰዎችን አስገድሎ ወደሥልጣን የሚረማመድም እንደማይኖር ካሁኑ ማስገንዘብ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ በምርጫ ሽፋን አመፃ አቀጣጥሎ የዋሆችን ገብሮ የሚገኝ ሥልጣን ቢኖር በጠባቧ የከርቸሌ ክፍልህ ውስጥ ብቻ የሚታጠር መሆኑ አይቀርም፡፡ ይህን የነውጥ አባዜ የተጠናወታቸውና የመንግሥትን ሕግ የማስከበር ችሎታ የሚፈትሹ ተቃዋሚዎች በውል መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በአገራችን ለሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ውድድር ከበቂ በላይ ቦታ ባለበት ወደሁከትና ትርምስ ማምራት ወቅቱም፣ አገሪቱም፣ ሕዝባቿም የማይፈቅዱት ጉዳይ እንደሆነ ማስተዋል ያሻል፡፡ የአገራችን ሰው ‘‘ሳይቃጠል በቅጠል‘‘ የሚለው ቃጠሎ ለማንም ስለማይበጅ ነው፡፡ እሳት ... አፈር ... እሳት ከመሆን ራስን ለሕግ ልዕልና አዘጋጅቶ የሰከነ የፖለቲካ ጨዋታ ብቻ መጫወት ይበጃል፡፡ የባዩሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም ነውና ነገሩ፡፡